# ★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅጽ 34 ቁጥር 8 ሰኔ 2001 ዓ.ም.


## ወስፌ ሲለግም ቅቤ አይወጋም፤ ትግል ካልጠና ድል አይመጣም

ከተማው ጨለማ፤ ሀገር ሁሉ መከራና ዋይዋይታ ሆኖ ባለበት ነገ ቀን ፀሐይ ቢወጣም ቀን አልወጣልን ብሎ እየተሰቃየን ፍዳ ስንጋት፤ ስቃይ ስንቀበል ጊዜ እያለፈ ነው። ወያኔ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ ከዓመት ዓመት የሕዝብ ኑሮ ይበልጥ ከባድና መራራ እየሆነ፤ የኢትዮጵያም ህልውና ለከፋ አደጋ እየተጋለጠ ቀጥሏል። በሥልጣን ያለው ጠባብ ብሔረተኛና ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን ሰማይ ከምድር ቢገጥም ከተያያዘው አጥፊ ተልዕኮ ከቶም ፈቅ የማይል መሆኑን አሳይቷል። ይህን ያረጋገጠውም የብዙ ዜጎችን ሕይወት ቀጥፎ፤ ብዙ ሺዎችን ለእስርና ስየል ዳርጎ በርካታዎችን ደብዛ አጥፍቶ ነው። ከ18 የመከራ ዓመታት በኋላ የወያኔን አገዛዝ ከዛሬ ነገ ይሻለው ይሆናል በሚል ብዥታ ማስተናገድ፥ ከስህተት በላይም ሀገርን የሚጎዳ ከባድ ጥፋት ነው።

መራራው ትግላችን የሚፈልጋቸውን መልሶች ለማግኘት በቅድሚያ ትክክለኛና ተገቢ ጥያቄዎችን መጠየቅ መቻል አለብን ። ጥያቄው አራምባ ከሆነ መልሱ ቆቦ መሆኑ የሚጠበቅ ነው። በገዢነት የሚሰየሙት ፀረ ሕዝቦች ደግሞ የሕዝብ ጥያቄ መሠረታዊ መሆኑን ትቶ በአልባሌ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር ለመጠምዘዝ ይጥራሉ። በመሆኑም በየጊዜው አዳዲስ መሰል ግን አወናባጅ የሆኑ ጥያቄዎችን ወደ መድረክ እየወረወሩ ውዠንብርን ያሰፍናሉ። በዚህ ተልዕኮ የወያኔ ቡድን ረጅም ልምድ ያለው በመሆኑ ተንኮሉን ማወቅ ያልቻሉና የተሞኙ ክፍሎች ለወያኔ ቡድን ሰለባ ሆነው ቆይተዋል። በአሁኑ ወቅት የወያኔ ቡድን ቁንጮ ሆኖ ሕዝብን ሲያስለቅስና ሲያስመርር የነበረው ግለሰብ ከያዝኩት ቦታ እለቃለሁ ሲል የለፈፈው የሕዝብ ዋና መወያያ ጉዳይ እንዲሆን የወያኔ አገዛዝ ይፈልጋል - የሌባ ዓይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ ነው ነገሩ። የኢትዮጵያ ምልዓተ-ሕዝብ ጥያቄ አረመኔው አገዛዝ ከነግሳንግሱ ከሀገራችን ምድር ተወግዶ እንዲጠፋ ሆኖ ሳለ፥ ለገሰ በአድህኖም መተካቱ ፋይዳ ቢስ ነው። ሀገራችን ዛሬ የሚያስፈልጋት የጉልቻ መቀያየር አይደለም፤ የዘረኞችን ምድጃ ፈነጋግሎ መጣል እንጅ! ፀረ ሕዝቡ አገዛዝ ከግንቦት 1997ቱ ምርጫ በኋላ የሕዝብን ድምፅ ሰርቆ በሥልጣን መቀጠሉ ዋናው ችግር ሆኖ እየተከሰተና የሕዝብ ድምፅ ይከበር፤ ሕገ ወጡ አገዛዝ ይውረድ የሚለው ዋና ጥያቄና መፈክር ሆኖ እያለ፥ በጥቃቅን ጥያቄዎች ላይ ማተኮርና መረባረብ፥ የሀገሪቱን መሠረታዊ ጥያቄ

አቅጣጫ እንዲስት ማድረግ ይሆናል። ዛሬ የትግላችን ዋና ጥያቄ የወያኔ አገዛዝ እንዴትና መቼ ይወገዳል ነው እንጂ፥ የቡድኑ ውስጣዊ መሽጋሸግ አይደለም። ለዚህም ነው የወያኔውን ዋና አረመኔ በሌላ ቅጂው መተካቱ ዋና ጥያቄ የማይሆነው። በዚህ መልክ ነው የ2002 የወያኔ ምርጫ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎትና ጥቅም አንፃር ስብ የለሽ ጉዳይ ሆኖ የሚታየው።

ራሳቸውን ብቸኛ የሕዝብ ድርጅትና መሪ ብለው የሚሰይሙ በዚሁ የትግሉን የትብብርና ቅንጅት ዕድል የሚያቀጭጩ ዛሬም ያሉ ቢሆንም ትግላችን ካልጠናና ካልተጠናከረ ወደ ድል እንደማይደርስ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው። በዛው ልክ ግን ማነው ወዳጅ ማነው ጠላት የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ መመለስ ሳይሆን፥ መጠየቁም የተሳናቸው ክፍሎች የትግሉን ይዘትና አቅጣጫ ውል አስተው ሲያንገላቱትና ሲያደናብሩት ባጅተዋል። የመጀመሪያው ጥያቄ ኢትዮጵያና ሕዝቧ ለደረሰባቸው ሁሉ ማነው ተጠያቂ የሚለው ሲሆን ጥፋትን በየትከሻው ለመስቀል የሚደረገውን ሩጫ አስቁሞ ለሀገራችን ስቃይ ዋናው ተጠያቂ የወያኔ አገዛዝ መሆኑን መቀበል ያስፈልጋል። ዛሬ ብዙሃኑ የወያኔን አገዛዝ ፀረ ኢትዮጵያነት በተመለከተ ምንም ብዥታ ባይኖራቸውም ሰይጣኑ ቀንዱና ጭራው እየታየ መልዓክ ሊሉት የሚከጅሉና ከወያኔ ቆሻሻ ጫማ ስር ወድቀው ሊሰግዱ ደፋ ቀና የሚሉ መኖራቸው ምስጢር አይደለም። የባርነትና የውርደትም ወልፍ አለው፤ በሽታውም ይጋባል። ስለሆነም ባንዳዎች፥ አድርባዮችና ተለጣፊዎች ሌሎች አጎብዳጆችን እየወለዱ በትግል እሳት ላይ ውሀ ያፈሳሉ። የሕዝብ ዋና ጥያቄና ዕይታ በዋናው ጉዳይ ላይ እንዳይሆን ለማድረግ ሲማስኑም ነጋ ጠባ ግራ አጋቢ መፌክሮችን እያስተጋቡና ሳርን አሳይተው ገደሉን ሲሸፍኑ ነጋ ጠባ የሚታለልላቸው ከበረከተ የጭቆና አገዛዝ ዕድሜውም እንዲሁ ይራዘማል። ተቃዋሚ ኃይሎች በዚህ ወጥመድ ሲያዙም ዋና ትኩረታቸው በዋናው ጠላት ላይ መሆኑ ቀርቶ በእርስ በርስ መለስተኛ ልዩነቶች ላይ ይሆንና እርስ በርሰ ሲናከሱ ዋናው ጠላትም ይህን ልዩነት እያራገበ ሁሉንም ያዳክማል፤ የጋራ ትግላቸውንም የውሀ ሽታ አድርጎ ያስቀረዋል።

የወያኔ ቡድን ለሥልጣን ከመብቃቱ በፊት በጋራ መክሮ የወሰነው የሁሉም ብሄረሰብ የመገንጠል ግዴታ አቋም ህብረ ብሄራዊ ትግሉን ምን ያህል እንደጎዳው ቢያንስ በአሁኑ ጊዜ ያልተረዳ የለም ማለት ብንፈልግም፥ ተንኮሉን ተረድተው ስምሪታቸውን ያላስተካከሉ አሁንም ጥቂቶች አይደሉም። የወያኔ ቡድን በራሱ ቁጥጥር ስር በሰኔ 1983 የሽግግር ጉባዔ ሲያካሂድና ተቃዋሚ ኅብረ ብሔራዊ ኃይሎችን ሲያግድ ፀሐያችን አበራች ብለውና በብሔረሰብ ደረጃ ተደራጅተው ፀረ ሕዘቦቹን ያጀቡ ጥቂቶች አልነበሩም። እነኢሕአፓ ጦረኞች ናቸውና በዚህ ጉባዔ አይገኙም፤ ከልክለናል ሲል እሰየው አሉ። የወያኔ የድርጅት ጦር የሽግግሩ መንግሥት ጦር ይሆናል ሲላቸው እጃቸውን ሰቅለው ድጋፍ ሰጡ። የግንጠላ ፈንጂውን ሲቀብር ጉድጓድ አብረው ቆፈሩ። ኢትዮጵያ ለቅርጫ ስትቀርብ ካራቸውን ይዘው ተኮለኮሉ። ኅብረ ብሔር ድርጅቶችን አግልሎና ኢትዮጵያዊነት ላይ በጭካኔ ዘምቶ የግንጠላንና የርስ በርስ ጥላቻን መርዝ እየጋተ ሕዝብንና ድርጅቶችን ሲከፋፍል አብረውት የሞኝ ገበሬ እርሻ በሰኔ የሆኑት ክፍሎች ሁሉ ውሎ አድሮ

ምሳቸውን ተቀብለው ከመድረኩ ተሽቀንጥረዋል ወይም ማስመሰሉን ትተው በይፋ ተለጣፊ ሆነው ተዋርደዋል። ወያኔ፥ ዋናውን የዴሞክራሲ መንግሥት ጥያቄ ወደ ጎን በማድረግና የብሔረሰብ ጥያቄን ከዚሁ ነጥሎ ወደፊት በማምጣት ጠባቦችን በጥበታቸው እየኮረኮረ ከጎኑ አሰልፎ ሊጠቀምባቸው ቻለ። ዕብድ ለዕብድ አብሮ ይነጉድ እንዲሉ ኢትዮጵያን የካዱና በጠባቡ የተቃኙ አብረው ከነፉ። ጉዞው ግን የእኩልነት አልነበረምና የወያኔ ቡድን የሽግግር መንግሥት ጦር ይሁን የተባለውን ጦር ይዞ፣ አፋኝ ተቋሞችን በቁጥጥሩ ስር አስገብቶ ብቸኛ የበላይነቱን ለማስፈን ግራ ቀኙን ቀጠፈ። ጠላት በተባለው አማራ ላይ ወያኔን አጅበው ነፍጠኛ፥ ትምክህተኛ ብለው ያጓሩትንም ተራ በተራ የባለጌ ጡጫ መታቸው። ወይኔ ቢሉ ጊዜው አልፏልና፣ ሊያግዟቸው ይችሉ የነበሩት በወያኔ ሲጠቁና ሲጎዱ አብረው በሞኝነት አጨብጭበዋልና ታዳጊ አላገኙም።

የወያኔ ቡድን ሰሚ ጠፍቶ እንጂ እኛ ሥልጣን ከያዝን ሕዝብ ፈልጎናል ማለት ነውና ሌሎች ፓርቲዎች ይታገዳሉ ብሎ ፅፎ ነበር። በ1982 በቶሮንቶ በተካሄደው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ጉባዔ ላይ አልገኝም ካለ በኋላ በኦሕዴድ ስም ባወጣው መግለጫ በቶሮንቶ የተገኙት ድርጅቶች ሁሉ "የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲጨቁኑ የነበሩ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ደግሞ ባርነትን ጭነው በትምክህተኛ ተግባራቸው ማንነቱን ሊያጠፉ ሲጥሩ የነበሩ ናቸው" ብሎ ሁሉንም ትምክህተኛ በሚል ከሶ ነበር። የመገንጠል ጥያቄ ያነሱ ክፍሎችም በ"ሕዝባቸው" ዘንድ በዚሁ ጥያቄ ላይ ውሳኔ ሕዝብ ወይም ሬፈረንደም ማካሄድ አለባቸውም ብሎ ነበር። የወያኔም ቁንጮ በዚያኑ ጊዜ (ኖቬምበር 28/1989) ለእንግሊዙ ዘ ኢንዲፔንደንት ለተባለው ጋዜጣ በሰጠው ቃለ መጠይቅ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች የመገንጠል መብታቸው ይከበርና ይገንጠሉ በኋላ የሚፈልጉ እርስ በርስ ይዋሃዱ ማለቱም ይታወሳል። የሽግግሩ መንግሥትም እንዲቋቋም የብሔረሰብ ጥያቄ "በሬፈረንደም ብቻ ነው የሚፈታው የሚል ቃልና ዋስትና መስጠት አለበት" ሲልም ወያኔ ፅፎ ነበር። ይህን መሰል የወያኔ ልፈፋ በተመለከተ ኢሕአፓ፥ ለምሳሌ በነሐሴ 13/1990 ባወጣው መግለጫ ("እሰጥ አገባው እስከመቼ") በዝርዝር ምላሽ ሰጥቶ ነበር። የወያኔ መሰሪ ቡድንም በወቅቱ በእርግጥ ለማደናገርና ለማወናበድ ብዙ ውሸቶችን በሁሉ አቅጣጫ ማሰማቱ የሚታወቅ ነው። ኢሕአዴግ የሚል ጭምብል አጥልቆ የተወሰኑትን ቢያደናግርም በመሠረቱ የጠባብ ብሔረተኛ አቋሙን፣ የማስገንጠል ዕቅዱን ክዶ ወይ ደብቆ አያውቅም ማለት ይቻላል። ጥፋቱ አልሰማ ያሉ ጆሮዎች ባለቤቶች ጋ ነው ብንል ስህተት አይሆንም። ወያኔ የተመሰረተበት የግንጠላና ፀረ ኢትዮጵያ አቋም መቸም የማይለወጥ ሆኖ ሳለ የማደናገሪያ ከበሮውን በደለቀ ቁጥር አብረውት የሚዘሉት ሁሉ ለትግላችን መዳከም ተጠያቂ ናቸው። ዛሬም የወያኔ ቁንጮ ቦታውን መልቀቁ ዋና ጥያቄ ነው ብለው ሊያሳምኑን እየጮኹ ናቸው። ይህን አጠቃላይ ሁኔታ በተመለከተ በሚያዝያ 1987 በዴሞክራሲያ እትም (ቅፅ 18/ ቁጥር 1) የሚከተለው ሰፍሮ ነበር፣

> *" ጭጋጉ በመግለጥ ፈንታ ደይኑ ጥቅጥቅ ብሏል። የቀድሞዎቹ ገዢዎች ለፍፁም ሥልጣን ሲባዝኑ ኖረዋል። የዛሬዎቹ ግን ፍፁም ሥልጣንን ሀገርን ከእነ ጭራሹ*

*ከማዋረድና ከመበታተን ጋር አቆራኝተው የሚራመዱ ከመሆናቸው ሌላ ወደ ሥልጣን ያደረጉት ጉዞ የንፁሀንን ሬሳ እየደቀደቀ የዘለቀ፤ ለዓመታት ለሕዝብ ልዕልና ሲታገሉና መከራ ሲቀበሉ የነበሩ ታጋዮችን (የኢሕአፓ ሠራዊት አባላትን) ደም በማፍሰስ የታጀበ ነበር። ባላደገበትና ባልበቀለበት ከሕወሓት ዴሞክራሲን መጠበቅ ከየዋህነት ያለፈ ክስተት መሆኑ ቢታወቅም ኢሕአዴግ የተባለው ቡትቶ ምን መሆኑን መረዳት የተሳናቸው፤ መዘወሪያቸው በባዕዳን ተይዞ ሀገርን የካዱ ክፍሎች፤ በጠባብ አመለካከት ዓይናቸው አርቆ ማየትና መመልከትን ትቶ የቅርቡን፥ የዛሬውን ሹመትና ወንበርን ብቻ ያዩ ግለሰቦችና ቡድኖች ለወያኔ የማደናገሪያ፥ የማጭበርበሪያ ፖለቲካ ለሆነው የሽግግር ሂደት፤ ለጥፋት ተልዕኮው ቀጥተኛና መለስተኛ መሳሪያ ሆኑ"።*

ከዚህም ተያይዞ መጪውን ምርጫ ተብዬ ፋይዳ ቢስ ሂደት በተመለከተ ዋናው ጉዳይ የወያኔ ፀረ ዴሞክራሲ አገዛዝ መቀጠሉ፤ የምርጫ ሕግና ኮሚሽኑ አለመቀየሩ፥ ወዘተ፥ .... ወዘተ ሆኖ ሳለ በ2002 ወያኔ ፍትሀዊ ምርጫ የሚያደርግ ይመስል፥ የሚለፈፈው የሐሰት ብዛት እውነትን ዋዛ ሊያደርግ እየቃጣ ነው። ወያኔና ተለጣፊዎቹ ለዚህ ምርጫ ተብዬ በሕዝብ ላይ የሚቀልድ ሂደት ለማድረግ ሲዘጋጁ፥ ይህንን ለማጀብ ደግሞ፥ ከየስርቻው ብቅ ያሉ ከሀዲዎችና ከርስ አደሮች ተለጣፊነታቸው ማጠየቂያ ልዩ ልዩ ምክንያቶችን እየደረደሩ ናቸው። በ97ቱ ምርጫ የተፈጁት ዜጎች ደም የፍትህ ያለ ጩኸቱን ሳያቆም፤ በዴዴሳ፥ ዝዋይ፥...ወዘተ የተወረወሩትና የሚሰቃዩት ወገኖች ሳይፈቱ፤ የወያኔ አገዛዝ በወንጀሉ ቀጥሎ ሀገርና ሕዝብን በሁሉም መስክ እየጎዳ ባለበት ሀገር ሰላም ነው፤ ሁሉም ጫታ ነው፤...ወዘተ ብሎ ወያኔን በምርጫ ለማጀብ መነሳት በሀገር ላይ በደል መፈፀም ነው። ወያኔ በጨበጨፋቸው ንፁሃን ዜጎች ደም መቀለድ ነው። የመጣ ቢመጣ ብሎ በዚህ ፀረ ሕዝብ ቀልድ አልሳተፍም ማለት ከሀገር ወዳድ ኃይሎች ሁሉ ይጠበቃል። ዋናው ጥያቄ ህጋዊ የተባሉት ቡድኖች በራዲዮና ቴሌቪዥን የመናገር ዕድል አገኙ/አላገኙም የሚለው አይደለም። ዋናው ጥያቄ የሕዝብን ድምፅ ሰርቆ በሥልጣን የቀጠለው ቡድን ዛሬም ተመሳሳይ ውንብድና ሊፈፅም ዝግጁ ሆኗል የሚለው ነው። ነገሩ ሥርዓትን፥ አገዛዝን ይመለከታል።

የግለሰቦች ሚና እንዳለ ሆኖ ግለሰቦች ሚዛናቸው ቀሊል ነው። የወያኔ አገዛዝ ደግሞ የተጠመቀበትና ያደገበትን ፀረ ሕዝብነትና ጠባብነት እንዲሁ በቀላሉ የሚተወው አይደለም። ለደደቢት ዛር ጠበሉ፥ መድኃኒቱና ማርከሻው፥ ወያኔ የሚፈቅደው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል የማይሆነው ም ለዚህ ነው። የወያኔ አገዛዝ በሁሉም መስክ ክሰረትንና ቀውስን ተከናንቧል። ዛሬ በአዲስ አበባ ሳይቀር መብራትና ውሀ እንኳን ጠፍቷል። የኑሮ ውድነት ጣሪያ የሚባል ከነበር ሰብሮ ከበረረ ወራት አልፈዋል። ፋብሪካዎች እየተዘጉ ሠራተኛው ወደ ሥራ አጥነት እየተወረወረ ሲሆን፤ ብርም ዋጋው ወርዷል። በቀን ሦስቴ አበላችኋለሁ ያለው ቡድን፥ ለራሱ ስድስቴ እየበላ ከአስር ሚሊዮን ያላነሰውን ዜጋ ለረሀብና ለጠኔ ዳርጓል። የባለሥልጣኖቹ ሙስናና ዋልጌነት የሀገሪቷን የሥነ ምግባር ልምድ እያደባየ ነው። ማኅበረ-ሰባዊ ሕጎች

ፈራርሰው ፥ ወንጀሎች፥ አሳፋሪና ባለጌ ድርጊቶች በመስፋፋት ላይ ናቸው። የድህነቱ ስፋትና ጥልቀት የዜጎችን ሰብዕና ፅናት እየተፈታተነ ነው። ሀገሪቷ ለባዕዳን መጫወቻና ብዝበዛ ተጋልጣ ተሰጥታለች። ዘወትር ቀና መመኘት የሚቀናውና፥ ከእባብ እንቁላል ርግብ ሲፈለፈል ለማየት የሚጓጉ ቢሆን፥ ከ18 ዓመት ግፍና መከራ በኋላ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያን ሊያጠፋ የመጣ መዓት መሆኑን መካድ አይችልም። ስለዚህም ዋናውና ትክክለኛው ጥያቄ፥ ወያኔ ይሻሻላል ወይም ይለወጣል የሚለው ሳይሆን፥ በምን ያህል ፍጥነትና እንዴት ይወገዳል የሚለው ነው። ከላይ በተጠቀሰው ዴሞክራሲያ አስፍረነው የነበረው ሌላ ሀቅ ዛሬም እውነታነትና ወቅታዊነት አለው፤

*"ከጠረሩ አድማስ፤ ብቅ እንዲል የሚጠበቀው የብሩህ ቀን ጮራ አልፈነጥቅ ሲል፤ ጨለማው ከክረምት ጨለማ ሲከፋ፤ ሁኔታዎች ሲጠጥሩ እንደ ቁጤማ እጥፍ ለሽ፤ ጎበጥ ለመጥ የሚሉ አይጠፉም። ለምን ለሚለው ጥያቄ የየራሳቸውን ምክንያቶች አጥተው ሲጨነቁና ሲጠበቡ ታይተው አይታወቁም። የሕዝባችን ረጅምና መራራ ትግል፤ ብዙ ታጋዮች ሕይወታቸውን የሰውለት ዓላማ ምንነቱ ካልተዘነጋ ፤ ክቡርነቱ ካልተሳተ በስተቀር በአቋራጭ በአምባገነኖች ጫማ ስር መውደቅ የሚታሰብ አይደለም። የትግሉ ግብ ከግል ጭቆና ወደ "ሻል ያለ" ወይም "ለስለስ ያለ" ባርነት ለመግባት፤ በሺ የሚቆጠሩትን መቀበርን ወደ መቶዎች ቀብራ ለመቀየር፤ ዛሬም መብት አልባ ሆኖ ግን ከትላንት "በተሻለ" መብት አጤነት ለመገኘት አይደለም። በሂደት ለሚገኝ ለውጥና በተደጋጋሚና ተደራራቢ ድሎች ያለን እምነት እንዳለ ሆኖ በመሠረታዊ ጥያቄዎቻችንና በሕዝብ ልዕልናና ባለመብትነት ላይ የሚደረግ ማንኛውም ገደብ የሚጎረብጠን መሆኑ አያጠራጥርም። ....በአሁኑ ወቅት ደግሞ ከዴሞክራሲ ጥያቄ ሌላ የሀገራችን ህልውናና አንድነት ከመሠረታዊም በላይ ዋና ጥያቄ ሆኖ እያለ ይህንንም ሆነ፤ በ"ትንሽ" ና በ"ትልቁ" መደፈሩን የማንቀበለውና የማንደራደርበት ነው።"*

ዋናው ጥያቄ የዴሞክራሲ ሥርዓት መስፈኑ ከሆነና በወያኔ ማንነት ላይም ግልፅና ትክክለኛ ግንዛቤ ከተያዘ ምን ማድረግ አለብን ለሚለው ጥያቄ ምላሹ ምስጢር ሊሆን አይችልም። በእርግጥ ቀደም ሲል ወያኔ ይህንን ጥያቄ ለማፈን ሲል ሕዝብ ጦርነት ሰልችቶታል፤ መንገዱ የሰላማዊ ትግል መንገድ ብቻ ነው በማለትና ይህ ሰላማዊ ትግል የተባለውንም በወያኔ ስር ተኮልኩሎ፤ ሕገ መንግሥቱ የሚለውን በሞላ ተቀብሎ፤ በወያኔ ፍቃድ ድምቢጣዊ ድምፅን አልፎ አልፎ በ"ጨዋ" ተቃውሞ ማሰማት በሚል ተርጉሞ ትጥቅ ትግል ያሉትን ሁሉ ቅጥረኞችን ፈልፍሎ ነበር ። ሰላማዊ ትግል ወይስ የትጥቅ ትግል የሚል በምትህት ግምብ የተለያየ ስልትን በመድርክ አውጥተው በጉንጭ አልፋ ክርክር ያስጠፉት ጊዜ ትንሽ አልነበረም። ሕዝባዊ አመፅና ትጥቅ ትግል በሁለገብ ትግል እቅፍ ውስጥ ያሉና የሚቀናጁ መሆናቸውን የሚክዱ ህሳዊ መሲሆች ይህን የወያኔ ተልዕኮ ሊያሚሉ ያልፃፉት፥ ያልጮኹትና አልፎ ተርፎም ያላወገዙት ታጋይ ኃይል አልነበረም። በጊዜ ሂደትና በትግል ይህ ብዥታ ተወግዶ ዛሬ ብዙኃኑ የወያኔ

አገዛዝ በኃይል ካልሆነ በሰላም የሕዝብን ድምፅና ፍላጎት እንደማያከብር ያመነበት ሁኔታ እውን ሆኗል። ቢሆንም በአልሞት ባይ ተጋዳይነት የሁለገብ ትግል ፀሮች ይህን የትግል መንገድ የተቀበሉ መስለው አፋዊ ድጋፍን እየሰጡ በተግባር ግን የሰላም ትግል የሚሉትን ማለትም በወያኔ ጫማ ስር ወጣም ወረደም መደፋትን እየገፉና እያራመዱ ናቸው። ጥያቄው በሰላም ወይ በሌላ ሊሆን የማይችልበት ዋና ምክንያት፥ በሰላም ከወያኔ ጋር መታገል፥ እኛ በተመክሮ እንዳየነው በቅዠት ደረጃ የሚፈረጅ በመሆኑም ነው። የወያኔ አገዛዝ በአስቸኳይ--ዛሬ ሳይሆን ትላንት--መወገድ ያለበት ነው። በቆየ ቁጥር ሀገሪቷን መቀመቅ እያወረደ የሕዝብን መከራ ያባብሳል።

ስለዚህም 18 ዓመት የተፈተነ መንገድ ሁሉ ወደምንፈልገው መዳረሻ አልሰደደንምና--አልሰራምና-- ፍቱን ሊሆን የሚችለውን የሁለገብ ትግል አስቀድሞ መገኘቱ ምርጫ የሌለው ግዳጅ ነው። ይህ እንዴት እንታገል የሚል ጥያቄ በዚህ መልክ ትክክለኛውን ምላሽ ሲያገኝ ደግሞ ይህ ትግል ሊጠናከርበት የሚችልበትን ሁኔታ ታጋዮቹ የመፈለግና የማግኘት መብታቸውን በመፃረር የጎንዮሽ ጉዳዮችን አጉልቶ በመቅረብ ሁለገብ ትግሉን ለማደናቀፍና ተብትቦ ለማክሸፍ የሚደረጉትን ጥረቶች ሁሉ መታገልም ያስፈልጋል። በወያኔ ሥርዓት፥ ተወደደም ተጠላም የፖለቲካ ሥልጣን የሚወለደው በምርጫ ሳጥን ብቻ ሳይሆን በትጥቅ ትግል በታጀበ ሕዝባዊ አመጽም ጭምር ነው። በዚህ በኩል የራሳችን ሰፊና ክቡር ተመክሮ አለን። ከባዕዳን ጭቁኖችም ትግል መማር እንችላለን። ከነገረ ቀደም፥ ማወቅ፥ መገንዘብና ማመን ያለብን ግን፥ የመጀመሪያው ህቅ ያለ መራራ ትግል ስርየትና መብት የማይገኙ መሆናቸውን ነው። ካልታገልን በሥልጣን ያለው ቡድን ይንቀናል፤ ይኩራራል። ወያኔ አንዱን ሕገ ወጥ አዋጅ በሌላ እያጀበ የሚጨፍርብን ያለምክንያትአይደለምና ኢትዮጵያዊ ወኔ አለመሞቱን በትግል ልናሳምነው ይገባናል።

ወሰፌ ከለገመ ቅቤን አይወጋም። ሕዝብ አምርሮና ቆርጦ ካልታገለ ትግሉ አይጠናም። ትግሉ ካላየለ ደግሞ አረመኔው ቡድንም ሆነ የባዕድ ጡት አባቶቹ ሕዝብ እምቢ ማለቱን፤ መቆጣቱንና ሀገሩንና መብቱን ሊያስከብር መነሳቱን የሚያውቁበት መንገድ አይኖራቸውም።

ፀረ ወያኔ ትግላችን ይፋፋም!!